# ግጭት አስወጋጅ ወይስ ህቡዕ የሁከት አዘጋጅ?

**(ክፍል አንድ)**

**ሐሰን አባፊጣ**

ከመሰንበቻው አይጋ ፎረም የተሰኘውና አገር ወዳድ ዜጎች በስፋት የሚሳተፉበት ኢትዮጵያዊ ድረ - ገፅ "Ethiopia after meles" /ኢትዩጵያ ከመለስ በኋላ/ የሚል ፅሑፍ አስነብቦን ነበር።

ፅሑፉ የቀረበው አቶ ጌታቸው መኳንንት በተሰኙ አገር ወዳድ ዜጋ ነው፡፡ በውስጡም ግለሰቡ አገር ቤት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ታላቁ መሪያችን አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበሩበት ወቅት ያከናወኑትን ተግባር በመልካም ሁኔታ የዓይን እማኝ ሆነው ያቀረቡት ነው።

የአቶ ጌታቸው ፅሑፍ በተለይም እንደ ግንቦት ሰባት ዓይነት ጥቂት ፅንፈኛ ፖለቲከኞች 'ኢትዮጵያ ከመለስ በኋላ እንዲህ ልትሆን ትችላለች' በማለት የሚያሚርቱትን አሳፋሪ ተግባር በግላጭ እርቃኑን አስቀርቶታል ማለት ይቻላል።

እነዚህ ጥቂት የጭፍን ፖለቲካ አራማጆች አገር ውስጥ ያልተፈጠረን ጉዳይ በስማ በለው በማውራት ላይ መሆናቸውን ከፀሐፊው ትንታኔ ብገነዘብም፤ የዚህ ፅሑፍ ዓላማ ግን የእነዚህን አሉባልተኞች ፍላጎት መቃኘት አይደለም።

ይልቁንም የፅሑፌ ማጠንጠኛ ዋነኛ ዓላማ ከእነዚህ የፅልመት ፖለቲከኞች ትርኪ ምርኪ ወሬዎችን እየቃረመ እንዲሁም በአገር ውስጥ በህቡዕ ካስቀመጣቸው "ቅጥረኞች" የተዛባ መረጃ እየተቀበለ በስመ "ግጭት አስወጋጅነት" በየጊዜው በአገራችን ላይ የጥፋት ናዳን የሚመኘው ዓለም አቀፍ የግጭት አስወጋጅ ቡድን /ICG/ ነኝ ባይን የሚመለከት ነው።

ሕዝቦች ወደ አላስፈላጊ ግጭቶችና አለመግባባቶች እንዳይገቡና ሠላማዊ መስተጋብር እንዲሰፍን ለማስቻል እንደሚሰራ ይሰብካል – ይኸው ራሱን "ዓለም አቀፉ የግጭት አስወጋጅ ቡድን" እያለ የሚጠራው የኒዮ ሊበራል አቀንቃኝ፡፡

ይሁን እንጂ ቡድኑ በተግባር የሚያደርገው በንድፈ ሀሳብ ካስቀመጠውና ከሚለፍፈው ያፈነገጠ ነው፡፡ ምግባርና ቃሉም አራምባና ቆቦ ናቸው፡፡ በዓለም ደህንነት እቆረቆራለሁ ቢልም በተጨባጭ እንደሚታየው ሕዝቦችን ከማቀራረብና የሚከሰቱ ችግሮችን ከማረም ይልቅ ነዳጅ ማርከፍከፍ የሚቀናው አፍራሽ 'ድርጅት' ነው፡፡

ታዲያ ይኸው ለሕዝቦች ደህንነትና ለዓለም ሠላም እተጋለሁ ባዩ ቡድን በቅርቡ ኢትዮጵያን በተመለከተ ሰፋ ያለ ዘገባ አስነብቧል፡፡ ዘገባ ከምንለው ሚርት አሊያም ቅዥት ቢባል ሳይሻል አይቀርም፡፡ አንድ

ኩንታል ሙሉ ፍሬ አልባ ልብ ወለድ ነው – ቢጨመቅ አንድ የሻይ ማንኪያ የምታህል ቁም ነገር የማይወጣው ተራ ሟርት፡፡

እንደ ቡድኑ ቅዥት ከሆነ ኢትዮጵያ ከታላቁ መሪያችን ህልፈተ ህይወት በኋላ ህልውናዋ ያከትማል፡፡ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊነት ተረት ይሆናሉ፡፡ በአጭሩ እንደምንበታተንና እንዳልነበረ እንደምንሆን ጠንቁሏል – እርግጥ የቡድኑ ይህን መሰሉ ተራ ልቦለድ ቅዠት እንጂ ነብይነት አሊያም መገለጥ አይሆንም፡፡

ይሁን እንጂ ቡድኑ እንዳሰበልን ሳይሆን እነሆ ቀናትና ወራት ነጎዱ፡፡ እንኳንስ ልንበታተን፣ እንደ እፍኝት እርስ በርሳችን ልንበላላ ቀርቶ ከማንኛውም ወቅት በላቀ አንድነታችን እየጠነከረና አብሮነታችን እየደመቀ መጥቷል፡፡ ለነገሩ ቡድኑም እውነታውን መመስከር ተስኖት እንጂ፤ በዚህ ዘመናዊ ዘመን ድሮም በአንድነታችን የማንደራደር ፍቅር የነገሰብን ሕዝቦች መሆናችንን ዘንግቶት አይመስለኝም፡፡

በእርግጥ ቡድኑ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጠልሸት ተግቶ ሲሰራ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደምም ተራ የመንደር አሉባልታዎችን እየቀራረመ የበሬ ወለደ ወሬዎችን ዘርቷል፡፡ ሰሚ ጆሮ አላገኘም እንጂ፡፡ በቅርቡ “ኢትዮጵያ ከመለስ በኋላ” በማለት ያቀረበው አስገራሚ ሪፖርትም የተለመደው የጥፋት አጀንዳው ቀጣይ ክፍል መሆኑ ነው፡፡

ከፀረ - ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ተሻርኮ የሚነግድ የጥፋት ቡድን በመሆኑ ውሸት ካልፈበረከ እንቅልፍ አይወስደውም፡፡ በበጎ ምግባር ስም የሚሰበስበውን ድጋፍም ሊያገኝ አይችልም፡፡ ዳሩ ግን ‘የተቋሙን’ና የጋሻ ጃግሬዎቹን የጥፋት መለኮት ተከትሎ ወደ ገደል

የሚፈረጥጥ ግልብ ትውልድ ባለማግኘቱ (መቼም አያገኝም) ቅዠቱ ቅዠት ሆኖበት ቀርቷል፡፡

ለጽሑፌ ማንፀሪያ ትሆነኝ ዘንድ ይህችን ታህል ካልኩኝ ዘንዳ ከቡድኑ ፍሬ አልባ ወሬዎች መካከል እየጠቃቀስኩ ትዝብቴን ልቀጥል፡፡ ሆኖም ዓላማዬ ከተገኘ አሉባልታ ጋር አብሮ መንጎድ ባለመሆኑ ከእያንዳንዱ ነጥብ ጋር እንካ ስላንቲያ ለመግጠም አልሻም፡፡ እናም በዚህ ከተስማማን ነገሬን ልቀጥል፡፡…
“አገሪቱ መረጋጋት እየራቃት መጥቷል” ይላል – የቡድኑ ግልብ ምልከታ፡፡ የአቶ መለስ ሞት ለትርምስ እንደዳረገንም ያትታል፡፡

እኔ በበኩሌ መረጋጋት እየራቃት የመጣችው አገር የትኛዋ እንደሆነች አልገባኝም፡፡ ቡድኑ ራሱ ስለ ማንና ስለ ምን እንደሚያወራ የገባው አይመስለኝም፡፡ “ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው” እንዲል የአገሬ ሰው የምር ስለ ኢትዮጵያ መረጋጋትና አለመረጋጋት እማኝነት መስጠት የሚገባን እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን ወይስ ባህር ማዶ ከአንዲት ካፌ ተቀምጦ “ሆት ዶግ” የሚገምጥ ህልመኛ ሰው፡፡ ፍርዱን ለውድ አንባቢዎቼ ልተወው፡፡ ሆኖም እኔ በግሌ ታማኝ መስካሪ ከእኛ ወዲያ ላሳር ባይ ነኝ፡፡

ሌላ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ካለች እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ የእኛይቱ ኢትዮጵያ ግን ቡድኑ እንደሚለፍፈው ሠላም አልራቃትም፡፡ አልተበታተነችም፡፡ በምንም መልኩ መቼም አንበታተንም፡፡ መበታተን ከነበረብን በደርግ ውድቀት ዋዜማ ላይ ነበር – ግና ምሥጋና ለታላቁ መሪያችን ይሁንና ያንን ወቅት በብልሀት ተሻግረነዋል፡፡

እርግጥ የታላቁ መሪያችን ሞት ቢያሳዝነንም፣ ውስጣችን በሀዘን ቢኮራመትም አንድነታችንን ግን አልፈታውም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው እኛ ኢትዮጵያውያን ከባለ ራዕዩ መለስ ዕረፍት በኋላ ይበልጥ ተሳስረናል፣ ተግባብተናል፡፡ አንድነታችን፣ አብሮነታችን፣ ፍቅራችን ጠንክሯል፡፡ ይበልጥ ተዋህደናል፡፡ ይህን መካድ ሀቅን መደፍጠጥ ይመስለኛል፡፡

ደግሞም አንድ ነገር መዘንጋት የለበትም፡፡ ኢትዮጵያ በታሪኳ የአንድነት ችግር ገጥሟት አያውቅም፡፡ ታሪክ ቢገለጥና ዶሴ ቢፈተሽ እርስ በርሳችን የተበላላንበት ዘመን አይገኝም፡፡ ቡድኑም ቢሆን ሀቅን ለመመስከር ሞራሉም ፍላጎቱም ስሌለው እንጂ እንደዘበት የምንናድ የእንቧይ ካቦች እንዳለሆንን ያውቃል – ቢያንስ በልቦናው፡፡

ያው ቅጥፈት ምግባሩ በመሆኑ ነው – እውነታውን ሸምጥጥ አድርጎ ክዶ አሉባልታን የሚያራግበው። እኛ ኢትዮጵያዊያን አንድነት ገደደን፣ አብሮ መኖር ከበደን ተብሎ ቢነገር እንደምን ይታመናል፡፡ ከራሳችን አልፈን ለጎረቤት ሕዝቦች ደህንነትና አንድነት፤ ሠላምና መረጋጋት የምንጨነቅ፤ ሠላም ወዳድ ሕዝቦች አይደለንምን? – እናም ግልፁን፣ ግጥጥና ፍጥጥ ያለውን ሀቅ መካድ አያዋጣም፡፡

እርግጥ እምነታችንም ሥነ - ምግባራችንም አንድነትን የሚሰብክ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል – ቡድኑ፡፡ በድፍን ዓለም መወደሳችን አንድም ለድፍን አፍሪካና መላው ዓለም አንድነትና ለሠላም የመታተራችን ድምር ውጤት መሆኑንም እንዲሁ፡፡

የዓለም አቀፍ የግጭት አስወጋጅ ቡድን ግን ይህን ያፈጠጠና የአደባባይ ሀቅ ለመስማት ጆሮ የለውም፡፡ እያየም አያይም፡፡ ለማየትም ለመስማትም አይፈቅድም፡፡ ባህሪውም ምግባሩም ስላይደለ አንድነታችን መበታተን ይመስለዋል፡፡ አዎ! ኢትዮጵያን ለማተራመስ የተደራጁ ጥቂት የጥፋት ኃይሎች የጡት ልጅ መሆን ስለሚዳዳው ገፅታችንን በተራ አሉባልታዎች ለማጠልሸት መቋመጡ የሚገርም አይደለም፡፡

አንዳንድ ጊዜ እንቅጭ እንቅጩን መነጋገር ደግ ነገር ነው፡፡ እናም ብንጨዋወት አይከፋም፡፡… እንዲያው ማን ይሙት የዛሬውን ትውልድ የአንድነት ጉዳይ ያሰጋዋል?፣ መለስ በመሞታቸው ተበታትነናል? - እንዲህ ያለው ነገር “አልሰሜን ግባ በለው” እንዲሉት ዓይነት ነው ነገሩ፡፡

ሕጻን፣ አዋቂ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከሊቅ እስከ ደቂቅ አውራው እንደተነካበት የንብ መንጋ በአንድነት ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያዘነውና እንባ የተራጨው ሆደ ቡቡና አዛኝ ሕዝብ ስለሆነ ብቻ አይደለም – በአብሮነት ያጋመደው አንዳች ረቂቅ መንፈስ በውስጡ ስላለው እንጂ፡፡

በእኔ እምነት በቡድኑ መዝገበ ቃላት ፍች እስካልተሰጠው ድረስ የአንድነታችንን ኃያልነት፣ ክብደትና ጥብቀት አብጠርጥሮ የሚያሳይ ረቂቅ ነገር ግን ተጨባጭ እውነት ከዚህ የበለጠ አሣማኝ አስረጅ የለም፡፡

አንድ ስለሆንን ነው በአንድነት ያነባነው፡፡ አንድ ስለሆንን ነው የታላቁን መሪያችንን ራዕይ ለማሳካት ያለምንም ቀስቃሽ ቃል የገባነው፡፡ አንድ ስለሆንን ነው የህዳሴያችንን ብሥራት የምናዋጅበት ቀንን ቅርብ ለማድረግ በልማት አብሮነታችንን አድምቀን ደፋ ቀና የምንለው።

ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ የቡድኑ ቅጥፈት የፖለቲካ ክስረት ይመስለኛል፡፡ ያሳፍራልም፡፡ በተጨባጭ እኛ ኢትዮጵያዊንና ሀቅን ለመጋፈጥ የሚደፍሩ ተቋማትና የዓለም ሕዝብ እንደሚመሰክረው በአንድነት እጦት፣ በአብሮነት ሥጋት እየተፍረከረክን አደለንም፡፡ እኛ ሥራ ላይ ነን፡፡ ዛሬ የምናወራበት ጊዜ የለንም፡፡

ለአንድነታችን ከሁለት አሥርታት በላይ ዓመታትን በጥበብ ካለፍናቸው ቆየን፡፡ እኛ በቀላሉ የምንረታ ተራ ጀሌዎች አይደለንም እንጂ፤ በችግሮች የምበረከክ ግልብ ፍጡራን ብንሆን ኖሮ ያኔ ድሮ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነትና ታሪክ በተደፈጠጠበት ወቅት በተለያየን ነበር፡፡

እናም ታጋዩ መሪያችን አቶ መለስ አንድነታችንን አጥብቀውት እንጂ አላልተውት አልሄዱም፡፡ በክፍል ሁለት ፅሑፌ ሌሎች የቡድኑን አስገራሚ አራምባና ቆቦ ዘገባ ይገፍላችሁ እመለሳለሁ።